
# ኩፍኝ

## ትንሽ ሽፍታ ብቻ አይደለም።



## የኩፍኝ በሽታ በተለይ ለህጻናት እና ለትንንሽ ልጆች አደገኛ ሊሆን ይችላል።

**የኩፍኝ ምልክቶች በዋናነት የሚከተሉትን ያካትታሉ:**

- **ከፍተኛ ትኩሳት** (ከ104°F በላይ ሊጨምር ይችላል)
- **ሳል**
- **የአፍንጫ ፍሳሽ**
- **ቀይ እና/ወይም እንባ ያኮተሩ አይኖች**
- **ሽፍታ** (ምልክቶቹ ከጀመሩ ከ3-5 ቀናት በኋላ ይታያል)

## ኩፍኝ ከባድ ሊሆን ይችላል።

የኩፍኝ በሽታ የሳንባ ምች፣ የአንጎል እብጠት (ኢንሰፍላይትስ) እና ሞትን ጨምሮ ከባድ የጤና ችግሮች ያስከትላል።

**ከ5 በኩፍኝ የተያዙ ሰዎች1** ሰው ሆስፒታል ይገባል።

**ከ20 የኩፍኝ በሽታ ያለባቸው ህጻናት1** ህፃን በትናንሽ ልጆች ላይ በቀዳሚነት በኩፍኝ መሞት የሚስከትለው የሳንባ ምች ይይዛቸዋል።

**ከእያንዳንዱ 1,000 የኩፍኝ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ውስጥ 1** ሰው የአንጎል ውስጥ እብጠት ያጋጥመዋል፣ ይህም ወደ አንጎል ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።

**ከ1,000 የኩፍኝ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ውስጥ 1 እስከ 3** የሚሆኑት ይሞታሉ።

**ኩፍኝ በጣም ተላላፊ ነው**
እና የታመመ ሰው በሚያስል ወይም በሚያስነጥስ ወቅት በአየር አማካኝነት ይተላለፋል። አንድ የኩፍኝ በሽታ ያለበት ሰው በአካባቢው ካሉ 10 ያልተከተቡ ሰዎች ወደ 9ኙ ሊያስተላልፍ ይችላል።



## የኩፍኝ በሽታን ለመከላከል ከሁሉ የተሻለው መንገድ ክትባት ነው

አንድ ልጅ ከ12-15 ወር ላይ እና ከ4-6 አመት ላይ የኩፍኝ-የጆሮ ደግፍ-ሩቤላ (የጀርመን ኩፍኝ) (MMR) ክትባት መውሰድ አለበት። የሁለት ጊዜ ክትባቶች በኩፍኝ ለመከላከል 97% ውጤታማ ናቸው።

የCDPH የክትባት ክሊኒኮች ለሁሉም የቺካጎ ነዋሪዎች አገልግሎት ይሰጣሉ። የነዋሪነት ማረጋገጫ እንዲያሳዩ ሊጠየቁ ይችላሉ።
**CHICAGO.GOV/VACCINES**

ሌላ የክትባት አቅራቢን ለመለየት እርዳታ ከፈለጉ፣ እባክዎን ይጎብኙ:-
**VFC.ILLINOIS.GOV/SEARCH/**

CDPH
Chicago Department of Public Health

**CHICAGO.GOV/MEASLES**